# General Relief Society Meeting
# September 24, 2011

ልግስና አይወድቅም

በስልቪያ ኤች ኦልሬድ

የሴቶች መረዳጃ ማህበር አጠቃላይ ፕሬዘደንት የመጀመሪያ አማካሪ

ባለቤቴና እኔ በቅርቡ የኢሎነይ ከተማ ናቩን ጎበኘን። እዛውእያለን የነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ብሮ የነበረበት እላይኛውቀዩ ሸክላ እቃቤት ቁጭ ብለን ነበር። እዛ በታዳግመኛ የተመለሰውን ታሪካዊ ሁነታ ከልብ አዳመጥን።

የሴቶች መደራጃ ማህበር የፈጠረውን እና እህቶች በዝሁ ክፍል ከነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ የተቀበሉትን አንዳንድ ትምህርቶች አሰብኩኝ። ይህ ትምህርት የሴቶች መደራጃ ማህበር የተገነባበት መሰረታዊ መሪህ ሆነ። እምነት የማዳበር አላማ፣ የፅዮን ቤተሰብን ማጠናከር እና የተቸገሩትን መርዳት የሴቶች መረዳጃ መህበር ስቋቋምነበር። ይህም በትንቢታዊ ተቀዳሚነት ያለውሁል ጊዜ የማይለወጡናቸው።

በነኻያ ቅድሚያ ስብሰባዎች ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ጳውሎስ ለኮረንትያን የፃፈውን ጠቅሶ ነበር። ጎይለኛነትያለውስለ ፍፁምፍቅር ትምህርቱ እምነት፣ ምኞት እና ፍፁምፍቅር ከሆኑት ታላቅነትያለውግን ፍፁምፍቅር መሆኑን ጳውሎስ ገለፁ።

በፍፁምፍቅር የያዘውን ጥራት እንድህ አለኡ፣

"ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንምያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤

"…የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንምአይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤

"ከእውነትጋር ደስ ይለዋልእንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤

"ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።

"ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም"[2]

ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ለእህቶች እንድህ አሉ፣ ስለ ጎረቤታሁ አስተሳሰብ በልግስና ወሰን አይኑራችሁ……እንደ ኢየሱስ ካደረጋችሁ ነፍሳችሁን ሌለሎች ማስፋት አለባችሁ። ምግባረ ጥሩነታችሁን፣ ደግነታችሁን በመጨምር ልባችሁ ይዳብር። ወደ ሌሎች ሰፋ ይበል፣ በሰውልጆች ጥፋትና ስህተት ፍፁም ታጋሽ መሆን አለባችሁ። የሰውልጆች ነፍስ ዕንቁ ነው።

በመፅሀፍ ቅዱስ መግለጫ፣ ፍቅር የማይወድቅ ስለሆነ የሴቶች መረዳጃ ማህበር መፈክር ሆነዋል። ምክንያቱም ይህን ትምህርት የደገፈ ነው። ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ለሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች ድሆችን በመርዳት ነፍስ እንድያድኑ ታዛዝ ሰጣቸው። [4]

ይህ በተፈጥሮ የሴቶች መረዳጃ መህበር ሥራ በመሆኑ መሰረታዊ ትምህቱ በአለምደረጃ መሉ ተቀባይነት አግኝተዋል።

ፍፁምፍቅር ምንድነው? እንዴት ማግኘት እንችላለን?

ነቢይ ሞርሞን ፍፁምየሆነ የክርስቶስ ፍቅር ብለውገልፀዋል። ጳውሎስ እንዳስተማረውየ ፍፁማን መተሳሰር ብለውገልፀዋል። ኔፍ እንደምያስታውሰን ሁሉምሰዎች ፍፁምየሆነ ፍቅር እንድኖራቸውየጌታ ትዕዛዝ እንደሆነ ገልፀዋል። [7]

ስለ ፍፁምፍቅር የጳውሎስ ቅድሚያ ትርጉምበመዳሰስ ፍፁምፍቅር በአንድ ድርጊት የምንሰጥ ሳይሆን የልባችን ሁነታ፣ በቸርነት ስሜት ፍቅርን በሚፍጥር ድርጊት የሚያሳይ ነው።

ሞርሞንም እንደምያስተምረው ፍፁምፍቅር እውነተኛ የጌታ ተከታዮች ለሆኑት እንደተሰጠ መሆኑን ነው። ይህን ላላቸው ፍፁምፍቅር ያነፃል። [8] በተጨማሪም ፍፁምፍቅር የተሰጦስጦታ ስለሆነ በመፈለግ ፀሎት ማድረግ አለብን። የስሌስትያል መንግስትን ለመውረስ ፍፁምየሆነ ፍቅር ልኖረን ይገባል። [9]

ጌታ እራሳችንን “ፍፁምበሆነ የመተሳሰር ፍቅር እንድናለብስ ጠይቆናል።”[10] ፍፁምፍቅርን ለማዳበር ምን ጥራት ልረዳን እንደምችል መጠየቅ አለብን።

ፍፁም የሆነ ፍቅርን እንድኖረን እና እንደ ኢየሱስ ለመሆን መጀመሪያ ፍላጎት ልኖረን ይገባል።

የሚቀጥለው ደረጃ መፀለይ ነው። “እንድንጸልይ ሞርሞን ይጋብዘናል፣ በዚህ ፍቅር ትሞሉ ዘንድ በኃይል ከልባችሁ ወደ አብ ፀልዩ፤ ይህ መለኮታዊ ፍፁም የሆነ ፍቅር ነው።” በዚህ ፍቅር ስንሞላ “እንደ እሱ እንሆናለን።”[11]

በየቀኑ መፅሀፍ አዱስ ማንበብ ሀሳባችን ወደ አዳኝ በማምጣት እንደ እሱ ለመሆን ፍላጎት ያሳድርብናል።

በቢሮየ Minerva Teichert titled *Rescue of the Lost Lamb*. የሚለውን ሥዕል ሰቀልኩኝ። አዳኝ ትንሹን በግ በክንዱ ይዞ በመሀከላቸው መቆሙን ያሳያል። “በጎቹን መግቡ”[12] የሚለውን ልመናውን እንዳስታውስ ይረዳኛል። ይህም ማለት ለኔ በአከባቢያችሁ ላሉት መስበክ እና ለተቸገሩት ልዩ ትኩረት ማድረግ እንደሆነ ያሳየኛል።

ፍፁም የሆነ ፍቅርን እንደት መዘርጋት እንዳለብን አዳኝ ፍፁም የሆነ ምሳሌያችን ነው። ለተራቡት፣ ለሀጢተኞች ፣ ለተጎዱት፣ እና ለታመሙት ርህራሄን አሳይተዋል። ለደሀና ሀብታም፣ ለሴቶች፣ ለልጆች፣ ለወንዶች፣ ለቤተሰቡ፣ ለጓደኞቹ እና ለንግዶች ስብከት አድርገዋል። ለከሳሾቹ ምህረት አድርገዋ። እናም በመስቃየት ለሰውልጆች ሁሉ ህይወቱን አሳልፈዋል።

ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝም በህይወቱ መሉ ፍፁም ፍቅርን በመከተል የወንድማማችነትን ፍቅር በመዘርጋት ሌሎች ክብር አሳይተዋል። እሳቸውም በቸርነት ርህራሄነት እና ሌሎች ሀሳብ እንዳለቸውየታወቁ ነበሩ፣

ዛሬም የፍፁም ፍቅር ምሳሌ ነቢይ ስለአለን የተባረክን ነን። ፕሬዝዳንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን ለአለምና ለኛ ምሳሌ ናቸው። እሳቸውም የፍፁም ፍቅር ልግስናን ለብሰዋል። ቸርነት እና ርህራሄ አላቸው። እና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሰባክ ናቸው።

ፕሬዝዳንት ሞንሰን እንዳስተማሩን፥ “ፍፁም ፍቅር ለጎዱን ሰዎች ታጋሽነት መኖር መሆኑን በቀላሉ ሆደ መሆንን መቋቋምን ነው። ደካማነትን እና ስህተት መቀበልን ነው። ሰዎችን እንዳሉ መቀበልን ነው። ከጊዜ በኋላ እየደበዘዘ ከሚመጣው አካላዊ ሰውነት ውጭ መመልከት ነው። ሌሎችን ከመዳኘት መቆጠብን ነው። ”13

ፍፁም ፍቅር ስኖረን ተመቺ ጊዜ ባይኖርም ሌሎችን ለማገልገል ፍቃደኛ በመሆን እናም ከለመታወቅ እና መለወጫማግኘትን ሀሳብ አይኖርብንም። ለመርዳት ትዛዝ አንጠብቅም ምክንያቱም ፍጽሱም ፍቅር በተፍጥሮአዊነት እንድናደርግ ያደርገናል። ቸርነት፣ እንክብካቤ፣ ለጋሽ፣ ታጋሽ፣ ምህረት፣ ሌሎችን መጨምር እና ከራስ ወዳድ ውጭ ለመሆን ስንመርጥ በፍፁም ፍቅር እንድተሞላን እንረዳለን።

የሴቶች መረዳጃ ብዙ በሆነ መንገድ ሌሎችን ይረዳል። አንደኛውአስፈላጊ የሆነ ፍፁም ፍቅርን የመለማመድ የሴቶች የጉኝት ትምህርት ነው። ውጤታማ በሆነ የጉብኝት ትምህርት ለማፍቀር፣ ለመስበክ እና ሌሎችን ለማገልገል ብዙ ዕድል ያጋጥመናል። ፍቅር ማሳየት ነፍሳችን በማንፃት አንደ አዳኛችን ለመሆን ያደርገናል።

በአለማት ደረጃ በጉብኝት ትምህርት አማካኝነት ወሰን የሌለውን ፍቅር በማየት እደነቃለሁ። ታማኝ የቤት ሌቤት ጉብኝት ለሚያደርጉ እህቶች የምለውበምታደርጉት ትንሽ የፍቅር ድርጊት አዳኝን በመከተል በመርዳት፣ በመንከባከብ፣ በማፅናናት፣ በማዳመጥ፣ በማበርታት፣ በማስተማር፣ እና በማጠናከር በጁ መሳሪያ ናችሁ። የዝህ አይነት ትምህርት አጭር ምሳሌ ላካፍላችሁ።

ሮዛ በስኳር በሽታና ሌላ የደከመች ናት። ከጥቂት አመታት በፍት የቤተክርስትያን አባል ሆነች። እሷምባል የሌላት አንድ ጎረምሳ ልጅ ነበራት። በተደጋጋሚሆስፒታል ትተኛ ነበር። ርሕራሄ ያላቸውየቤት ሌቤት አስተማሪ እህቶች እሷን ወደ ሆስፒታል ከመውሰድ እና ልጇን እቤት ከመጠበቅ ይልቅም ወደ ሆስፒታልም ሄደውያፅናኗት ነበር። የቤት ለቤት ጎበኝ አስተማሪዎች እንደ ጓደኛና ቤተሰብ አገልግለዋል።

ከጥቂት ጉብኝት በኃላ ይህች እህት መንበብ እንድማትችል እና መማር እንደምትፈልግ ካት ተረዳች። ምንም እንኳ ጊዜ እና ታጋሽነት እንደምጠይቅ ብታውቅም ካት እንደምትረዳት ቃል ገባች።

ኤምል እውነትን የምትፈልግ ወጣት ምስት ነበረች። በለቤቷ ሚካኤል ስለሀይማኖት ብዙ ፍላጎት አልነበረውም። ኤምል ታማሆስፒታል በነበረችበት ካል የሴቶች መረዳጃ እህት ምግብ በመውስውድ ልጅ በመጠበቅ፣ ቤትም በማፅዳት ኤምል የክህነት ሥልጣን ቡራኬ እንድታገኝ አደረገች። ይህ የፍቀር ድርጊት የሚካኤልን ልብ አለሰለሰ። የቤተክርስትያን ሰብሰባ ለመካፈል እና ከሚስዮኖች ጋር ለመገናኘት ወሳኔ ላይ ደረሰ። ኤምል እና ሚካኤል በቅርቡ ተጠምቆ ነበር።

ፍቅር ውድቀት አያሳይም፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር የማይገባውን አያደርግም፣ ፍቅር ሁሉን ነገር ይተነፍሳል፣ ፍቅር ሁሉን ነገር ይወጣል።

ፕሬዝዳንት ሄነር ቢ አይርንግ እንዳሉት፣ “የሴቶች መረዳጃ ማህበር ታሪክ እራስ ወዳድ ባልሆነ ውአስደናቅ አገልግሎት የተሞላ ነው። ...ይህ ህዝብ ከውነተኛ ጌታ ቤተክርትያን ብቻ ከምመጣው ቃል ኪዳኖችን በመጠበቅ የመጣ የሴቶች ውህደት ነው። የፍቅር ስሜታቸው የመጣው ከርሱ የጎጢያት ክፍያ ነው። የፍቅር ድርጊታቸው በምሳሌው የተመራ ነው፣ እናም ወሰን በለለው የርሱ የምህረት ስጦታ ምስጋናም ነው። እናም መንፈስ ቅዱስን ለአገልጋዮቹ በመላክ በምህረት ተልዕኮአቸውን እንድረዳ ያደርጋል። በዝህም ምክንያት የራሳቸውነገር ባይሳካም ያልተለመደውን ነገር ለሌሎች በማድረግ ደስታን ፈልገዋል። ”14

አገልግሎት በማድረግ እና ሌለሎች ፍቅርን በዘርጋት የራሳችን ችግርን ለመወጣት በመርዳት አነስተኛ ፈተና እንድሆን ያደርጋል።

አሁን ወደ ጥንቱ ዳግመኛ መመለስ ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ለእህቶች ያስተማረው ልመለስ፣ ስለ ፍፁምፍቅር እና ቅንነት እንድህ አሉ፣ “ይህን ትምህርት ካሟላችሁ በስሌስትያል መንግስት ወሮታችሁ ምንኛ ታላቅ ነው!! ልዩ መብታችሁን ከተከተላችሁ መላዕክት የናንተ ባልደረባ ከመሆን አይቆጠብም። ”15

በጥንቱ እንደ ናቹ ወቅት እህቶች የተቸገሩትን እንደረዱ ዛሬም እንድዝሁ ይኖራል። እህቶች በመንግስተ ሰማያት ለመንፈሳዊ ጥንካሬ መሰረት ናቸው።

ትጋት ያለው የቤት ለቤት ጉብኝን እርስ በርስ እንድረዳዱ ያደርጋቸዋል። የአዳኝን ምሳሌ በመከተል እሱ ያደረገውን ያደርጋሉ።

ሁሉም የሴቶች መረዳጃ ማህበር ሴቶች በፍቅር በመሞላት ትንሽ የሆነው የእነርሱ ፍቅራዊ ድርጊት ሌለሎች የማዳን ሀይል እንዳለው ማወቅ ይኖርባቸዋል። በእርግጠኝነት ፍፁም ፍቅር የክርስቶስ ፍቅር መሆኑን እና በፍፁም እንደማይወድቅ መሆኑን ያውቃሉ።

የሴቶች መረዳጃ ማህበር ታሪክ ስታነቡ ጠቃም የወንጌል መመሪያ በመፅሀፉ ሙሉ እንደምገኝ ታውቃላችሁ።

ለሁሉም የቤተክርስትያን ሴቶች ፍፁም ፍቅር የሆነው የክርስቶስ ፍቅር ስጦታ እንድሞሉ የልመና ግብዥ አጥቃልላለሁ። ደግን ለማድረግ ሁሉን አናሳሽ በመጠቀም በአከባቢያችሁ ላሉት እና ለቤተሰባችሁ ደህንነትን አምጡ። ጌታ ለጥረታችሁ በረከቱን ያደርጋል።

አባትና ልጁ ለኛ ያላቸውን ታላቅ ፍቅር ዕውቀታችን እና የሀጢያት ክፍያ እምነትና ምስጋናችን በአከባብያችን ላሉት ፍቅር እንድናዳብር ፍላጎት ይስጠን። ይህም ፀሎቴ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።